በላጩን ሥራችሁ፣ ንጉሳችሁ ዘንድ የጠራችውን ሥራችሁ፣ ደረጃችሁንም ከፍ የምታደርገውን ስራችሁን፣

ከአቡ ደርዳእ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "በላጩን ሥራችሁ፣ ንጉሳችሁ ዘንድ የጠራችውን ሥራችሁ፣ ደረጃችሁንም ከፍ
የምታደርገውን ስራችሁን፣ ለናንተ ወርቅና ብር ከመመፅወት የሚበልጥላችሁን ስራ፣ ጠላቶቻችሁን ተገናኝታችሁ አንገታቸውን
ከምትመቱበት አንገታችሁን ከሚመቱበት ስራችሁም በላጩ የሆነውን ስራ አልነግራችሁምን?" ሶሐቦችም "እንዴታ!" አሉ። እርሳቸውም
"አላህን ማውሳት ነው።" አሉ።»
[ሶሒሕ ነው።] [ቲርሚዚ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባልደረቦቻቸውን እንዲህ በማለት ጠየቁ ልዕለ ኃያሉ ንጉስ አላህ ዘንድ በላጩን፣ የላቀውን፣ የፋፋውን፣ የፀዳውንና የጠራውን ስራችሁን እንድነግራችሁ ትፈልጋላችሁን ጀነት ውስጥም ያለውን ደረጃችሁን ከፍ የሚያደርግላችሁን ስራስ ማወቅ ትፈልጋላችሁ? ወርቅና ብር ከመመፅወትም ለናንተ የሚበልጥላችሁን? ከከሀዲያን ጋር ለውጊያ ተገናኝታችሁ አንገቶቻቸውን ከምትቀሉና አንገቶቻችሁንም ከሚቀሉ የሚበልጠውን ስራ ማወቅ ትፈልጋላችሁን? ሶሐቦችም: አዎ ይህንን ማወቅ እንፈልጋለን አሉ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሁሉም ወቅትና በአጠቃላይ ሁኔታዎች ላይ አላህን ማውሳት ነው አሏቸው።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/3575